# ቴዲ ተፈታ አሉ!

ከነቅዓ ጥበብ



ቴዲ ተፈታ አሉ፣ መች ቴዲ ተፈታ፣
ያሰረው ነው እንጅ፣ ያገኘው እፎይታ።

ቴዲ ተፈታ አሉኝ፣ ሰማሁ ጥሩ ወሬ፣
እንኳንስ ደስ አለሽ፣ ኢትዮጵያ ሀገሬ፤
እንኳን ደስ አላችሁ፣ ወገኖች በሙሉ፣
የተሟገትክለት፣ የተሰለፍክ ሁሉ፣
በተለይ እናቱ፣ ቴዲን ያበቀሉ።

የፍቅር፣ የሰላም፣ ያንድነት አቀንቃኝ፣
ከጨለማው ወጣ፣ ከክፉ ዓለም በቃኝ፣
የቴዲ አመክሮ፣ በጣም የረቀቀ፣
እንኳን በሱባዔው፣ በምህላ አለቀ፤
ኪነት ደስ ይበልሽ፣ ለቴዲ ዘምሪ፣
ለሃቅ መቆምሽን፣ ዛሬም አስምስክሪ፣
ቴዲን የመሰሉ፣ ጀግኖችን ፍጠሪ።

ቴዲን ነፍሰ-ገዳይ፣ የሚለው ሰው ማነው?!
ቴዲ ያዳከመ፣ መጠላላትን ነው!
ቴዲ የገደለ፣ መለያየትን ነው!

የቴዲን መፈታት፣ ጥላሁን ቢሰማ፣
ዕድሜው በረዘመ፣ በሙታን ከተማ።

በሙታን ከተማ፣ ህያው በጠፋበት፣
ሙት ለሙት ተቃቅፎ፣ በሚላቀስበት፣
እባክህ ቴዲ አፍሮ፣ እሥትንፋስ ዝራበት።
ወገንህ በሙሉ፣ ሃጢአቱን እንዲያውቀው፣
ያሥተሠርያልን፣ ደጋግመህ ዘምረው፣
“ምከረው! ምከረው! ምከረው! ምከረው!
አልሰማ ያለውን፣ መከራ ይምከረው።”
የሞተውንም ነፍሥ፣ እግዚአብሄር ይማረው፣
ብርቱም እንዲትወጣ፣ ከጨለማው ቤት፣
አበራሽ እንዲንል፣ ባካል ስናያት፣
አደራ እንዳትረሽ፣ ኪዳነ ምህረት።